*Hesed multimedia*

# ኤክሌዢያ

ተጠርተው የወጡ ማለት ነው

17th Edition

ልዩ ቆይታ ከዶ/ር ዳዊት እና ከዶ/ር ኤልቤቴል ጋር



counseling team presents

August 2021


"How good and pleasant it is when God's people live together in unity!"
Psalms 133:1

# Hesed multimedia

EKKLESIA

WEDAJE LIBE

DAILY VERSE

Join us on telegram

**@juecsfcounseling**

# ማውጫ

HESED MULTIMEDIA

**EKKLESIA**

COUNSELING TEAM PRESENTS




1
**የ አዘጋጁ መልዕክት**
በዴቭ

3
**ኤክሌዢያ አፍታ**

13
**CHURCH FATHERS**
በሎሊ

18
**ንወራ**
በላዛ

23
**ምስባከ ሰባኪያን**
በአቤኒ

27
**ከዚህም ከዚያም**
በላዛ

31
**እንነጋገርበት**
በዶምቦ

33
**ጥበበ ሰማያት**
በወንዴ እና ሎሊ

35
**ይመልሱ ይሸለሙ**
በሜርሲ



ሰላም ሰላም FRESH ወንድሞች እና እህቶች እንዴት ናችሁ? እግዚአብሔር ፀጋውን አብዝቶላቹ ከብዙ ውጣ ውረድ በኋላ በሰላም ስለመጣቹ ደስ ብሎናል።ከብሉይ ኪዳን የሆነ ታሪክ ልንገራቹ። ያዕቆብ ወደ ላባ ቤት ሲሄድ ይመሸበትና ድንጋይ ተንተርሶ ይተኛል፤ በህልሙም ጫፉ ሰማይ የሚደርስ መሰላል በምድር ላይ ቆሞ፣ በላዩም የእግዚአብሔር መልአክት ሲወጡና ሲወርዱ አየ። የሕልሙ ፍቺ ምንድነው? ይህ ሰማይንና ምድርን የሚያገናኝ መሰላል ማንነው? እግዚአብሔር ፃዲቅ እና እውነተኛ ፤ ሰው ደግሞ ኃጥያተኛ ስለሆነ ኃጥያታችን ከእግዚአብሔር ለይቶን ነበረ።ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ማንም አይችልም ነበር ። ነገር ግን እግዚአብሔር በምሕረቱ ባለ ጠጋ ስለ ሆነ፥ከወደደን ከትልቅ ፍቅሩ የተነሣ በበደላችን ሙታን እንኳ በሆንን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር ሕይወት ሰጠን፥ በጸጋ አዳነን። አዎ ያዕቆብ ያየው ሰማይንና ምድርን የሚያገናኝ መሰላል ኢየሱስ ነው።(ዮሐንስ ወንጌል 1:52) ብቸኛው ወደ እግዚአብሔር አብ መሔጃ መንገድ እሱ ነው። በእዚህ ግቢ ቆይታችሁም ይህንን ታላቅ መዳን ይበልጥ እንድትረዱት ፤ ኢየሱስ ክርስቶስን በማመን እና በማወቅ እንድታድጉ ፀሎታችን ነው። ፀጋ ከእናንተ ገር ይሁን።

# 2011 fresh carnival



# ኤክሌዚያ እንግዳ

**ኤክሌዚያ፡ ለአንባቢያን ራሳችሁን አስተዋውቁ?**
**ዳዊት፡** ዳዊት ወርቁ እባላለው የህክምና ምሩቅ ነኝ።
**ኤልቤቴል፡** እኔ ኤልቤቴል እባላለው እኔም ሃኪም ነኝ።
**ኤክሌዚያ፡ ለቃለመጠይቁ ፍቃደኛ ስለሆናችሁ እያመሰገንኩ የመጀመሪያ ጥያቄዬ የሚሆነው ጌታን ከተቀበላችሁ ጀምሮ ዛሬ ላይ እስክትደርሱ ያለውን የእምነታችሁን ጉዞ በ አጭሩ አካፍሉን።**
**ኤልቤቴል፡** አመሰግናለው ያደኩት በክርስቲያን ቤተሰብ ነው እና ከ 10 አመቴ ጀምሮ መጽሃፍ ቅዱስ አነብ ነበር። ቤተክርስቲያን እሄድ ነበር ግን ብዙ አላገለግልም ነበር። ካምፓስ ከገባሁ ከመጀመሪያ አመት ጀምሮ ማለትም ከሱ ጋር መጽሃፍ ቅዱስ ማጥናት ከጀመሪኩ በኋላ ግን በብዙ በጸሎት፣ በአገልግሎት ማደግ እንደሚቻል አሳይቶኛል። መጽሃፍ ቅዱስ በደንብ እንዳጠና ፤ የመድረክ አገልግሎት እንድጀምር በብዙ አግዞኛል። ያው ከትዳር በፊት my spiritual mentor ነበር።
**ዳዊት፡** አመሰግናለው። እኔም ያደኩት በክርስቲያን ቤተሰብ ውስጥ ነው። በልጅነቴ በኳየር ውስጥ እሳተፍ ነበር። ነገር ግን የጌታን ነገር በደንብ በራሴ ያወኩት በሚሊኒየም የ7ኛ ክፍል ተማሪ እያለው ነበር። የጌታን ነገር ካወኩ በኋላ ብዙም ሳልቆይ የስብከትን አገልግሎት ህጻናትን በማስተማር ጀመርኩ። በዚህ ጊዜ ከ7 ወደ 8 ሳልፍ አካባቢ የእግዚአብሔር እቅድ ሆኖ የ12 ክፍል ተማሪ የነበረ ፋኑኤል ስዩም የሚባል spiritual mentor ጌታ ሰጠኝ።እሱ መንፈሳዊ አቅጣጫ አሳየኝ። እና በአብዛኛው ጊዜዬን ከክርስትና ኑሮ ባሻገር በአገልግሎት ነው ያሳለፍኩት።
**ኤክሌዚያ፡ ራሳችሁን physically emotionally እና spiritually እንዴት ነው ምትጠብቁት?**
**ዳዊት፡** physically: እኔ እዚህ ግቢ የምማርበት ጊዜ physically ራሴን እጎዳ ነበር። ብዙ ጊዜ ቁርስ አልበላም ነበር። ሳቅ… እንደውም እንሻ ተክሌ የሚባል ጓደኛዬ አንድ ጊዜ ቁጭ አድርጎ ለወደፊት ማገልገል ምፈልግ ከሆነ ዛሬ ራሴን መጠበቅ እንዳለብኝ መክሮኛል። አሁን ጌታ ይመስገን የምትንከባከብ ሚስት ስላለኝ በደንብ ነው ምበላው። ….ሳቅ… ። እና አሁን ደሞ ራሴን ለመጠበቅ ዋና ጀምሪያለው።



# ኤክሌዢያ ኤፍታ

Emotionally. የሚገጥመኝን ነገር በጾም እና ጸሎት በጌታ ፊት በማቅረብ ነው ምቆየው። የሚንከባከበውን የእግዚአብሔርንአባትነት እሱን ነው ምፈልገው።

Spiritually በጾም እና በጸሎት በመቆየት ፣ የእግዚአብሔርን ቃል በደንብ በማጥናት ፣የተመረጡ መጽሃፍትን በማንበብ እና በሳምንት የተወሰኑ ጥቅሶችን በማስታወስ እና በማሰላሰል ነው የራሴን መንፈሳዊ ቅርጽ ለመጠበቅ ምሞክረው።

**ኤልቤቴል**፡ physically ከባድ ጥያቄ ነው.... ሳቅ....በተመጣጠነ ምግብ አምናለው። እና ቤት ለማዘጋጀት ሞክራለው።

**ኤክሌዢያ፡ በቃ ቤት መጣለው።**

**ኤልቤቴል:** ሳቅ ..ና .... እና ምግብ በደንብ በላለው። ያው ሰሞኑን እየወፈርኩ ስለሆነ እንደሱ ዋና ጀምሬያለው።

Emotionally ያው እኛ ሴቶች ለ emotion ቅርብ ነን እና ራሴን የምጠብቀው ሃሳቤን በመጠበቅ ነው። የሚረብሸ መጥፎ ነገር እንዳላስብ እጠነቀቃለው። እና በከባድ ጊዜ ላይ ስሆን አንድ የእግዚአብሄር ቃል ይዤና ያንን አሰላስላለው።

Spiritually; ጸሎት ፣ የእግዚአብሄር ቃል እና አገልግሎት ። ቃል የለኝም እንዴት እንደጠበቁኝ።

**ኤክሌዢያ፡ አንዳችሁ ሌላችሁን በሁለት ቃል ብቻ ግለጹ**

**ኤልቤቴል** ፡ ብዙ ጊዜ እለዋለው። My Home

**ዳዊት፡** ሁለት ቃል እሺ የመጀመሪያው ጨዋ ሁለተኛው Godly

**ኤክሌዢያ፡ ህይወታችሁን በጣም የለወጠ አንድ ስብከት ወይም መጽሃፍ?**

**ኤልቤቴል** ፡ መጽሃፍ እኔ አመናፈሺው አትበለኝ እና ....ሳቅ.... መጽሃፍ ቅዱስ ብል ደስ ይለኛል።

ስብከት፡ የአለምነህ ስብከቶች በጣም ተጽዕኖ አድርገውብኛል።

**ዳዊት፡** የማልረሳው ስብከት 11ኛ ክፍል እያለው ክረምት ላይ የእኔ መንፈሳዊ mentor ፋኑኤል ስዩም የዕብራውያንን መልዕክት ያስተማረው ያ የማልረሳው ቀን ነው።

ከመጽሃፍ ደግሞ ያው መጽሃፍ ቅዱስ የማይነካ ስለሆነ ይቀመጥ እና በጣም የእኔን መንፈሳዊ ነገር የለወጠ መጽሃፍ የ Wayne Grudem systematic theology ነው። በጣም የነገረ መለኮት እይታዬን ያስተካከለ መጽሃፍ ነው።



**ኤክሌዢያ፡ ኦው ጥያቄው በጣም ደስ ይላል።**
**ዳዊት፡** ጥያቄውን ነው
**ኤክሌዢያ፡ እረ መልሶቹም … ሳቅ ..**
**ዳዊት፡** ኤልቤቴል ….ረጅም ሳቅ …..
**ኤክሌዢያ፡ አሁን ደግሞ ስለሁለታችሁ ፍቅር ትንሽ ልጠይቃችሁ? ኤልቤቴልን አይተሃት ወድጃታለው ብለክ ያስብክበት moment ምን ነበር?**
**ዳዊት እና ኤልቤቴል** ….ረጅም ሳቅ …..
**ዳዊት፡** 1ኛ አመት ላይ anatomy cadaver room ከተማርን እና ከሰራን በኋላ ሰብሰብ ብለን ለብዙ እያወራን ነበር እና የሚወራው ሃሳብ ለሴቶች ህክምና ከተማሩ በኋላ ከዛ ለልጅ ተብሎ ቤት መቀመጥ እና ልጅን ማሳደግ ልክ ነው አይደለም የሚል ነበር። እና ሌሎች ሴቶች ሁሉም ይሄ ሁሉ አመት ተምሬ እማ በጭራሽ አልቀመጥም ነበር ያሉት። እሷ ግን በጊዜው ለልጆቼ እና ለቤተሰቤ የፈለገ ያክል ብማረም ቤት ለመቀመጥ እና ልጆቼን ለማሳደግ እና ዋጋ ለመክፈል ፍቃደኛ ነኝ ነበር ያለቺው። እና በሰዐቱ በጣም ነበር impressed የሆንኩት። ቤት አስቀምጣታለው በሚል ሳይሆን ብዙ ዋጋ የከፈለችበትን ነገር ለቤተሰቧ ስትል ለመተው ፍቃደኛ መሆኗ ነበር impressed ያደረገኝ።
**ኤክሌዢያ፡ አንቺንስ?**
**ኤልቤቴል፡** እኔን ከባድ ነው ……..
**ዳዊት፡** እንዴ ጡንቻዬ ምናምን ትዝ አይልሽም?
**ዳዊት እና ኤልቤቴል** ….ረጅም ሳቅ …..
**ኤልቤቴል፡** ሂደት ነው እና እኔን በጣም የሳበኝ ለሁሉም ሰው እግዚአብሄር የሆነ ቦታ አለው ትልቅ ቦታ አለው። ለሱ ግን ሁሉ ነገሩ ነው። እና እግዚአብሄርን መፍራቱ ነው የሳበኝ።
**ኤክሌዢያ፡ ከ ኤልቤቴል የምትወድላት የሰውነት ክፍል?**
**ኤልቤቴል** ….ረጅም ሳቅ …..
**ዳዊት፡** በጣም ቢያሸማቅቀኝም ቁመቷን ወድላታው። በተጨማሪ ደግሞ አይኗን እና ፈገግታዋን በጣም ነው የምወድላት።



# ኤክሌዢያ እፍታ

**ኤክሌዢያ፡ አንቺንስ?**
**ኤልቤቴል ፡** እኔ እንኳን ብዙም ያው ታውቃለህ እንደምታየው ነው ….. ሳቅ………
**ኤክሌዢያ፡ ይሄ ቃለመጠይቅ ለመኳረፊያ ምክንያት መሆን የለበትም ….ረጅም ሳቅ …..**
**ኤልቤቴል፡** ይመስለኛል ትከሻው ደስ ይለኛል እንደቅጥነቱ አይደለም ሰፊ ነው ትከሻው …….. ረጅም ሳቅ …..
**ዳዊት እና ኤልቤቴል** ….ረጅም ሳቅ …..
**ኤልቤቴል፡** አፍንጫው ደስ ይለኛል
**ኤክሌዢያ፡ ለኔ ጌታን ካገኘው በኋላ መንፈሳዊ ህይወቴ ተቀየረ የምትሉበት ጊዜ**
**ኤልቤቴል፡** አስር አመት እያለሁኝ መጽሃፍ ቅዱስ ማንበብ የጀመርኩበትን ጊዜ ነው መንፈሳዊ ህይወቴ የተቀየረበት ጊዜ የምለው። ያኔ የጀመርኩት ለምንድነው መሰልህ ጎበዝ ነበርኩ እና ሳድግ obviously ሃኪም ሆናለው፣ አገባለው፣ ልጅ ወልዳለው ብዬ አሰብኩ እና
**ዳዊት ፡** obviously ብለሽ አሰብሽ?
**ኤልቤቴል፡** አዎ አይገርምም ….. ሳቅ …. ከዛ ይሄን ህይወት ብዙ ሰው ኖሮታል እና ምንድነው የህይወት ትርጉም ብዬ አሰብኩ። ያኔ ገና 10 አመቴ ስለሆነ ቤተሰቦቼን ከጠየኩኝ ይቺ ልጅ ወዴት እየሄደች ነው ብለው እንዳያስቡ ስለፈራው መንፈስ ቅዱስም ይመስለኛል በቃ ለዚህ ጥያቄ መልሱ መጽሃፍ ቅዱስ ነው ብዬ ወሰንኩ።



# ኤክሌዢያ ኢፍት



**ዳዊት፡** ለኔ ህይወቴን የቀየረ moment የሆኑ የተከታተሉ 3 ታሪኮች አሉ። 3ቱም አንድ አይነት ውጤት ነበራቸው። የመጀመሪያው 8ኛ ክፍል እያለው ለአገልግሎት የሆነ fellowship ላይ ስሄድ እንዳጋጣሚ ሆኖ በመሪዎች ስህተት እኔን እና ሌላ አንድ አገልጋይ ነበር የተጋበዙት። እና እኔ ቀድሜ ደርሼ ስለነበር ያኛው አገልጋይ( በኔ እድሜ የነበረ ነው) በቃ እሱ ይስበክ እኔ ጸልያለው አለ። እኔ የእግዚአብሄርን ቃል ሰበኩ እና ወረድኩ ከዛ እሱ መንፈስ ቅዱስን በመግለጥ አገልግሎት ሲያገለግል፣ መልዕክት ሲያመጣ፣ እጁን ሲጭን ሳይ ወጣት እኮ ነው እንዴት እንዲህ ያለ አገልግሎት በዚህ እድሜ አልኩኝ ሁለተኛው ደግሞ በጣም ብዙ ትችት እና አወዛጋቢ የነበረው ኢዮሳፍጥ የሚባል ወጣት ያገለገለው ካሴት በጊዜው ማየቴ ነው። ኢዮሳፍጥ ማለት አዳማ( ናዝሬት) ላይ አንድ ወጣት ጌታ ተናገረኝ እያለ የሚያገለግል ወጣት ነበር። በጊዜው አወዛጋቢ እና አከራካሪ የሆኑ ነገሮችን ትተን እኔን በጣም influence ያደረገኝ ነገር በጣም በልጅነት እግዚአብሄር ይናገራል እንዴ የሚለው ነበር። 3ተኛ ደግሞ የኔ መንፈሳዊ mentor ያልኩህ ፋኑኤል የዛው ሰሞን አከባቢ ላይ ቢሾፍቱ(ድብረዘይት) የ 12ኛ ክፍል ተማሪዎች ያዘጋጁት ክሩሴድ ነበር። እሱ ላይ ቆሞ ጌታ መልዕክት ተናግሮኛል በሁለት አብያተክርስቲያናት መካከል ያለ ቅራኔ አለ ጌታ እንድትታረቁ ይፈልጋል ብሎ ሲናገር ያ በኔ እድሜ ስብከት ብቻ ሳይሆን እንደ ትልልቅ ሰዎች መንፈስ ቅዱስን በመግለጥ አገልግሎት(“charismatic”) ማገልገል ይቻላል የሚለው ነገር ህይወቴን significantly ነበር የቀየረው።

**ኤክሌዢያ፡ በዚህ ዘመን መናገር የምትፈልጉት ሁሉም ሰው ዘንግቶታል እና መዘንጋት የለበትም በጣም የከበረ ነገር ነው የምትሉት ነገር**

**ዳዊት፡** አንድ ነገር …… ጾም። አሁን በfellowship ብቻ ሳይሆን በቤተክርስትያን ራሱ እጅግ በሚያሳዝን ሁኔታ ጾም ቁርስ መተው እየሆነ መቷል። በቤተክርስቲያን ታሪክ ወስጥ እንደዚህ አይነት ነገር የለም። ምግብ ሳይበሉ በጌታ ፊት ለረጅም ሰዐት መንበርከክ ሚባለው ነገር ከቤተክርስቲያን ጠፍቷል። ይሄ ደግሞ ትልቅ ልምምድ ነበር ለቤተክርስቲያን።

**ኤልቤቴል፡ መንፈሳዊ ትጋት**

# ኤክሌዢያ ኤፍታ

**ኤክሌዢያ: ከመጋባታችሁ በፊት Propose አድርገህላት ነበር እና እሷን surprise ለማድረግ ምን ያክል ተጨንቀህ ነበር ምን ያክልስ ተሳካልክ?**

**ዳዊት:** can I be honest with you surprise አደርጋታለው ብዬ አንድም ቀን አስቤ አላውቅም ነበር። በባህርይዋ በጣም curious ናት እና ነገሮችን ቀድማ ነው ምታየው። ስለዚህ ስወስዳት ይገባታል ብዬ ነበር። አስበው መጀመሪያ ፒራሚድ ሪዞርት ነበርን ከዛ ወጥተን ደግሞ አዱላላ ነበርን። እና በቃ ታውቅብኛለች ብዬ ነበር። ስለዚህ በዚህ ጊዜ እየጠበኩ የነበረው ሃሳቧ የሚሰረቅበትን ጊዜ ነበር። እና ሃሳቧ የሚውሰድበት ጊዜ ብዬ ያሰብኩት ልትፈራ የምትችልበት ጊዜ ነው። ስለዚህ የጅልባ ጫፍ ላይ እንድትቀመጥ አድርጊያት ስትፈራ እና ሃሳቧ ሲሰረቅ ጠብቄ ቀለበት ሳሳያት በጣም ነው የደነገጠችው።

**ኤክሌዢያ: እንዴት ነው ተሳክቶለታል?**

**ኤልቤቴል:** አዎ surprised ሆኜ ነበር። እንዳለው ትንሽ ጠርጥሬ ነበር ግን በደንብ ሳስበው ደግሞ አያደርገውም አልኩኝ። it is too early አልኩ። ምክኒያቱም ውሏችንን አውቀዋለው ከየት አምጥቶ በየት በኩል plan አድርጎ ብዬ ....

**ዳዊት:** ከየት አምጥቶ ምትልክ ደሃ ነው እያለችክ ነው ...... ሳቅ ......

**ዳዊት እና ኤልቤቴል**.. ረጅም ሳቅ....

**ኤልቤቴል:** ሳቅ.... አስር ብር በኪሱ ይዞ ከየት አምጥቶ ነው? ሳቅ...... እና ግን በቃ ብዙ ሰው surprised አልሆነችም ይሄው ቀሚስ ለብሳ ተዘጋጅታ አይደል እንዴ የሄደቺው ያለ ሰው ሁሉ አለ። actually ያኔ ጓደኞቼ ቀሚስ መልበስ አለብሽ እዚህ ድረስ ለመዝናናት መጥተን ምናምን ስላሉኝ ነበር የለበስኩት። እና እዛ moment ላይ ህይወቴ significantly ሊለወጥ እንደሆነ ገባኝ።እና ሚገርመው ስለደነገጥኩ እሺ እስክል ድረስ ቆይቻለው።

ዳዊት፡ ጉልበቴን እያመመኝ ነበር..... ሳቅ ... ክርስትያን ተንበርክኮ ስለሚጸልይ ነው የቻልኩት ...... ሳቅ...

**ኤልቤቴል:** ሳቅ.....እና በቃ ህይወቴ ሊቀየር ስለሆነ በጣም ነበር የደነገጥኩት። እና በጣም ምወደው ቀን ነው።



# ኤክሌዢያ አፍታ

**ኤክሌዢያ፡ የተጋባችሁት በጣም በጊዜ ነው። የስድስተኛ አመት ተማሪ እያላችሁ እና እንዴት ነው ቤተሰብ ያሳመናችሁት?**

**ዳዊት፡** የእኔ ሁለት ታላላቅ ወንድሞች ነበሩኝ 30 ቤት ውስጥ የነበሩ እና ሁለቱም የማግባት እቅድ አልነበራቸውም። እኔ ላገባ ብዬ የጠየኩት በ 23 አመቴ ነበር እና የ 5ተኛ አመት ተማሪ ነበርኩ። ግን ሄጄ ሳናግራቸው በቃ ወዲያው ነበር የተቀበሉኝ ምክንያቱም አገልጋይ ስለሆንኩ በእጮኝነት ብዙ ጊዜ መቆየት የለብኝም የጌታን ስም አሰድባለው ነበር ያልኳቸው። እግዚአብሄር ይመስገን የ6ኛ አመት ተማሪ ላይ የሚከፈለን ደሞዝ እኛን ማኖር ይችላል። እና ከ 1 አመት በኋላ የማግባት እቅድ አለኝ እና እናንተ ናችሁ ምትድሩኝ እኔ ምንም የለኝም አልኳቸው። ደስተኞች ነበሩ።

ኤልቤቴል፡ ያው እኔ ሴትም ስለሆንኩ ከባድ ነበር። ቤተሰቦቼ ትንሽ ብትቆዩ ብለው ነበር። ግን በደንብ ነገርናቸው እቅዳችንን እና ከተመረቅን በኋላ መጋባት ሊከብደን እንደሚችለም አስረዳናቸው። እና ያው ተረዱን። ሌላ ቦታ ብቻዋን ከምትሆን ከአጠገቧ አጋሯ ቢኖር ጥሩ ነው የሚለው ነገር አሳመናቸው።

**ኤክሌዢያ፡ እናንተስ ጋር እንዴት ሃሳቡ መጣ?**

**ዳዊት፡** ለጋብቻ እኔ አስቤ የነበረው የመጨረሻ አመት ከሚከፈለን ገንዘብ save አድርገን ከተመረቅን በኋላ ነበር። አንድ ቀን ግን 5ኛ አመት ተማሪ እያለን እሷ ደውላልኝ ማናግርክ ነገር አለ አለቺኝ። ከዛ አስታውሳለው ቢዝን ጁስ እየጋብዝኳት ለምን ጋብቻውን 6ኛ አመት ላይ አናደርገውም? ዶርም ውስጥ እያጠናው ይሄ ሃሳብ ልቤ ውስጥ ከበደ። እና የጌታ ሃሳብ ይመስለኛል አለችኝ። ይህን ስሰማ በጣም ነበር የደነገጥኩት። ምክንቱም ጌታ ተናገረኝ ብቻ ሳይሆን ያለቺኝ በጊዜው እንዳንጋባ የሚከለክል ነገር አልነበረም።ከዛ ወደ ዶርም ገባሁኝ እና በጌታ ፊት ተንበረከኩ። ጌታ ሆይ ከሷ ጋር የሚኖረኝ የመጀመሪያ አመት የትዳር ጊዜዬ ከባድ እንዲሆን አልፈልግም ነበር ያልኩት። ከዛ በኋላ ግን የጌታ ሰላም ነበር የተሰማኝ። በመቀጠል 5 የማማክራቸው ሰዎች መረጥኩ። የመረጥኳቸው የቤተክርስቲያን መጋቢዬን ፣ my spiritual mentor ፣ የቤተክርስቲያን ሽማግሌ፣ 6ኛ አመት የህክምና ተማሪ( ሃይላት) እና የተጋቡ ሃኪሞች(ጌርስ እና ኩሜ) ነበሩ። እና ሁሉም ያሉን ተጋቡ ይሄ መልካም ሃሳብ ነው ነበር።



# ኤክሌዚያ ክፍል

**ኤክሌዢያ፡ ከናንተ የእጮኝነት እና የትዳር ህይወት በመነሳት ለሌሎች ሰዎች ምን ትመክራላችሁ?**

**ኤልቤቴል፡** የፍቅር ግንኙነት በጣም demanding ነገር ነው። ብዙ ነገርህን ይይዝብሃል። ለብቻ ከመሆን ጋር በጣም ይለያያል። እና ሰዎች ራሳቸውን መንገዳቸውን ራዕያቸውን እርግጠኛ ሳይሆኑ አንዴ relationship ተገብቶ ብዙ ነገር ካሳለፉ በኋላ ራስን ማወቅ ሲጀመር የገባህበት ትዳር ህይወትህን የሚያመሰቃቅል ነገር ይሆንብሃል። ስለዚህ relationship በጣም አስበው፣ ተረጋግተው፣ ሳይቸኩሉ ፣ ሰዎችን አማክረው፣ ዙሪያቸውን አይተው ቢሆን ከምንም በላይ ደግሞ ጌታን ሰምተው ቢሆን መልካም ነው። በተለይ fresh ተማሪዎች በጊዜ ባይጀምሩ መልካም ነው።

**ዳዊት፡** የመጀመሪያው ነገር ሰው የህይወት መስመሩን ሳያውቅ በፍጹም relationship ውስጥ ባይገባ ብዬ አስባለው። እኔ እንደ ጌታ ፍቃድ ሆኖ በጊዜ ነበር የህይወት መስመሬን ያወቁት እና እጮኝነት ከመጀመራችን በፊት ነግርያት ነበር። አገልጋይ እንደምሆን፣ የአገልጋይ ህይወት ስላለው መከራ፣ ለአገልግሎት ከቤት መራቅ እንዳለ፣ መቸገር እንዳለ እና እሷም ይሄን አምናበት ነው የገባነው። በተለይ ደግሞ ወንዶች ራስ ስለሆኑ የህይወታቸውን አቅጣጫ የግድ ማወቅ አለባቸው። ሌላኛው ነገር ደግሞ ግቢ ወስጥ ላሉ ልጆች ምመክረው ነገር relationship ውስጥ sexual purity በጣም ከባድ ነው። ይህን ስናገር እኔ እና እሷ ግቢ በነበረን ግኑኝነት እግዚአብሄርን በማያከብር ነገር አልወደቅነም። ስንጋባ መኝታችን ንጹህ ነበር። ይሄ ማለት ግን ፈተናዎች አልነበሩም ማለት አይደለም። ስለዚህ በተቻለ መጠን ግቢ ውስጥ relationship ባይጀመር ከተጀመረም ቅድስና በደንብ ቢፈለግ መልካም ነው። ሶስተኛ ደግሞ relationship ሲጀምሩ ወጣቶች mentor የሚያደርጋቸው የቤተክርስቲያን ወይ ደግሞ ክርስቲያን የሚያከብሩት ሰው ቢኖር ጥሩ ነው። ሌላ ደግሞ የrelationship ጊዜ ማርዘም ጥሩ አይደለም። ቤተክርስቲያን ትንሹ 6 ወር ትልቁ 2 አመት ብላ ያስቀመጠችበት ምክንያት አላት።



# ኤክሌዢያ አፍታ

**ኤክሌዢያ፡ መጨረሻ ማስተላለፍ የምትፈልጉት ነገር ካለ።**
**ዳዊት፡** እኛ ሰማያዊ ተጓዦች ነን። The Pilgrim's Progress ( የመናኙ ጉዙ ) የሚለውን መጽሃፍ እንደ ህይወት ምሳሌ አድርገን ብንወስደው ብዬ አስባለው። ምንድነው እሱ ክርስቲያን ተጓዥ ነው። እየተጓዘ ያለው ከጥፋት ከተማ ወደ ሰማያዊ ከተማ ነው። ሁልጊዜ ይሄን መርሳት የለብንም። ትምህርት ቢሆን፣ ትዳር ቢሆን፣ ስራ ቢሆን፣ ልጅ ቢሆን ሁሉም ያልፋል። ስለዚህ የበለጠውን ነገር እንዳንረሳ። በዚህ አጋጣሚ The Pilgrim's Progress ( የመናኙ ጉዙ ) የሚለውን መጽሃፍ ጋብዝልኝ።
**ኤልቤቴል፡** እኔ ማለት የምፈልገው አኛ የራሳችን አይደለንም። እና የምንፈልገውን፣ ደስ የሚለንን፣ ቤተሰቦቻችን ደስ የሚላቸውን ልንኖር አይደለም በቃ። መስቀል ደስ አይልም ግን ደግሞ ተሸክመን እንድንጓዝ ተጠርተናል። ስለዚህ መብቴ፣ ፍላጎቴ፣ ማለታችንን እያቆምን ባይመቸንም የጌታን መንገድ መምረጥ ብንችል መልካም ነው።
**ኤክሌዢያ፡ ስለ ቃለመጠይቁ እጅግ አድርጌ አመሰግናለው።**
**ዳዊት እና ኤልቤቴል፡** እኛም እናመሰግናለን።



# DO YOU KNOW?

### *Bible Statistics*

Number of Books in the Bible: 66
Number of Chapters: 1,189
Number of Verses: 31,101
Number of Words: 783,137
Number of Letters: 3,566,480

### *Bible facts*

The world's largest Bible weighs 496 Kg.
There are a total of 188 named women in the Bible.
China is the largest producer of Bibles.
Mahershalalhashbaz is the longest word in the Bible.
The "Christian" word occurs 3 times in the New Testament.

# CHURCH FATHERS





## AUGUSTINE OF HIPPO

This one August day was charming, and in a garden full of life and peace, a man sitting under a fig tree with a gloomy face was sobbing over his own miserable state, and moaning bitter heartedly " and you, O lord, how long? How long Lord, will you be angry, forever? .." ; when he heard a child from a neighboring house chanting " tolle, lege; take up, read". He wondered if he ever known a children's song like it, as he found out there was none, he took it as a sign from God and rushed to his friend and randomly took up a manuscript from Paul from the books they had been reading. At once, his eyes landed on," not in rioting and drunkenness, not in chambering and wantonness, not in strife and envying.

But put ye on the Lord Jesus Christ, and make not provision for the flesh, to fulfill the lusts thereof." Roman's 13: 13-14. And in his own words "No further would I read, nor did I need; for instantly, as the sentence ended, by alight, as it were, of confidence flooded into my heart, all the gloom of doubt vanished away,". After this, the man was changed altogether and came to be known to us, as Augustine of Hippo, doctor of the church. This is one of the most well-known conversion stories, and is found in Confessions, an autobiographical memoir by Augustine, and the story of redemption of one of the most influential theologians of the church.

*" Thou hast made us for thyself and our hearts are restless till they find their rest in thee"*
*Augustine*

# CHURCH FATHERS





Aurelius Augustus was born in Tagaste, Numida (in modern day Algeria) in 354 A.D. to an upper-class family. His father patricus was an unbeliever and his mother Monica was a devout Christian, who had diligently sought after his early Christian education.

At the age of eleven, he was sent to a school at Madurus and at seventeen, he set off to school at Carthage to study rhetoric. There, as a young man he had lived a life of fleshy excesses and sexual indulgences. Later on, he began to develop a keen interest in philosophy and knowledge, as he immersed himself in the writings of Cicero, and gradually began to abandon his mother's religion. In its place he came to embrace Manichaeism, a dualistic religion that taught individuals to save themselves by seeking knowledge. And, as Manichaeism had proven intellectually unsatisfying, he turned to skepticism of the new academy, and then to Neoplatonism, which may have paved a way for his return to Christianity.

" *Complete abstinence is easier than perfect moderation* "

*Augustine*





In 373, he returned to his hometown after he completed his studies to setup a school of rhetoric, and taught some Manichaeism on the side. But after two years he relocated to Carthage, as his mother kicked him out of her house. However, in 383 he went to Rome to open a school there, but the circumstances there had turned out to be disappointing. In the midst of this, he was given a position as a rhetoric professor to the imperial court at Milan and moved there as the possessor of one of the most prestigious positions. Through all of this, he never laid off his life of indulgences, and his mother has never ceased praying for him, as he wrote in Confessions, it was when she had been praying and weeping for him that she saw a dream that kindled a hope in her, that he would come to where she is.

Shortly after he resettled in Milan, Monica followed him, to arrange a suitable marriage for her son, after his 15 years of affair with a woman who he deeply loved and had a son with named Adeodatus; and This led to a split in the relationship and emotional turmoil that sued after. Following this, his mother introduced him to Ambrose in Milan, a prose orator and preacher of the gospel. He initially was drawn towards him due to his rhetoric abilities and oratory skills; But later he would be influenced by his preaching, and this would play a big role in his return to his childhood faith. Adding to the emotional strains of forsaking his mistress and the continuous shift in philosophies, Augustine was struggling with himself, for years he had sought to overcome his fleshy passions and nothing seemed to help. In the midst of all of this, was his famous "garden" conversion; alas, once and for all occasioned the sealing of the chains of events that led to it.

"Give what you command and command what you will."
Augustine

# CHURCH FATHERS





Augustine's conversion had sent shockwaves through his life. He had to quit his professionalism and retreat to study Christianity and Neoplatonism. On Easter Sunday 387, his son and him were baptized by Ambrose. Following this, he and his son returned to Tasgate and by the time he reached his hometown, he had lost his mother and one of his closest friends. Soon after his son would die too and Augustine would sell all his patrimony except his family home, which he turned into monastery and started to live as a monk; but in 391 he would be ordained to be a priest in Hippo against his will. Only eight years after his baptism, in 395 he would be elected bishop of Hippo.

He became an eloquent preacher with >350 preserved sermons, though also a heedful pastor to his congregation leading a monastic life in the Episcopal residence. He preached the gospel to, and worked tirelessly to convince the people of Hippo to convert to Christianity.

He defended the teachings of the church and her theology against internal and external challenges, sometimes even overbearingly. He raided against Donatists, a Christian separatist sect created after the great persecution of emperor Diocletian, since they believed the catholic church had been compromised and her leaders had betrayed her; He championed the position of the Catholic church doctrine on the sacrament as "ex opero operato" and emphasizes the "invisible" church. One of his most notable theological controversies came from pelagius, a devout British monk, who taught about free will as the main ,perhaps the sole, cause of sin and salvation, that people need to exercise self-control and righteousness; And Augustine on the contrary, strongly stood firm on God's total sovereignty, "Original sin" as the source to sin and Grace as the lone way to be justified from it, in his series of treaties: on Grace & free will, on the Grace of Christ and on the original sin. Eventually, Pelagius was excommunicated by the church in 417.

*"Since it is God, we are speaking of, you do not understand it. If you could understand it, it would not be God.*

*Augustine*





He also wrote other works like On the Trinity, where his writing led to the clause filioque in the Nicene creed. In his book City of God, he defended Christianity against claims that, it had caused the Roman empire's downfall by Alaric, by turning eyes away from the Roman gods; but he argued it was due to the empire's past sins.

*" Mankind is divided into two sorts: such as live according to man, and such as live according to God. These we call the two cities... The heavenly city outshines Rome. There, instead of victory, is truth."*
Augustine

In 430 AD, a 76 years old Augustine died from a fever and his writings, which having survived the vandals raid miraculously, took over the torch of his contributions to the next generation and his theology has become one of the most pivotal to the Church.




**መብረቅይምታኝ ከዋሸሁ**

ከሰዓት ነበር በህዝብ ማመላለሻ መኪና ዉስጥ በግራ የኋለኛው መቀመጫ ጥግ መስኮቴን ከፍቼ ተቀምጫለው፥ ወፈር ያሉ እናት፣ገዘፍ ያለ ሰውዬ እና አንዱ ጓደኛዬ በቅደም ተከተል ተሰድረን ተቀምጠናል። በጣም ጠባብ ስለሆነ መስኮቱን የከፈትኩት ለንፋስ ማስገብያ ሳይሆን ደረቴ ጋር የደረሰውን ጉልበቴን እና ግማሽ ትከሻዬን ገንፍሎ ሚወጣበት ቦታ ለማበጀት መሰለኝ ግን ሙቀቱም መሰለኝ ያስከፈተኝ።እናም በተንቀሳቃሽ ስልክ ከአንድ ሰው ጋር እየተነጋገርኩ በነገርኩት ነገር ስላላመነኝ ያሳምናል ብዬ ባመጣኋት መሀላ ንግግሬን አሟሸው "መብረቅ ይምታኝ ከዋሸሁ" አልኩኝ። ከጎኔ የነበሩት እናት በድንጋጤ "በስማም በወልድ ምምምነነው ልጄ እንዴት እንደዚህ ይባላል? ኧረ ጉድ ነው ወራጅ አለ ወራጅጅ፤ ተው ልጄ ተው እንደዚህ አይባልም" እያሉ ወረዱ።እኔም ይቅርታ እማማ..ይቅርታ፤ ያው ያለ ቦታቸው አስደንብሬአቸው እንዲወርዱ ስላደረኩ ወይ ደሞ እነሱ ስህተት ነው ብለው ስለመከሩኝ መቀበሌን ለማሳየት ይሆን... ብቻ አላውቅም ለምን ይቅርታ እንዳልኩ ግን ብያለው በቃ!! እናንተም ካሁን አሁን መብረቅ ግማሽ ተጎልጉሎ የወጣውን ሰውነቱን በመስኮት ነጥሎ አነደደው እያላቹ አትጠብቁ፥ በሰላም ወርጃለው።
እነዚህ እናት ጋር ያለውን መስመር ያልያዘ ፈሪሀ እግዚአብሔርን ሳስብ ያስደንቀኛልም ያሳዝኑኛልም።

በብሉይ ኪዳን እስራኤላውያን አምላክነቱን በግልጥና በቅርብ ሆነው የተመለከቱ ስለነበር ለመጣው ጣጣ ሁሉ ባወጣን ያውጣን እያሉ ሙሴን ገፍተር እያረጉ ነበር እግዚአብሔርን ሚሰሙት(ዘፀ 20:18, ዘዳ 5:22, ዘዳ 19:16)፤እግዚአብሔር ሲናገርና ሲቆጣ ክብሩ ያስፈራቸው ነበርና። ካስተዋልን ግን የእግዚአብሔር መብረቅን ማንጎድጎዱ ወይ እሳት ማውረዱ አይደለም እንዲፈራ ሚያረገው(ምንም እንኳ ይህ ሲሆን ማስቲካ እያኘከ ሚቆም ባይኖርም)፤አምላካችን ፍጹም፣ጻድቅ፣ታላቅ፣ዘላለማዊ፣የሚታየውንና የማይታየውን አለማትና ፍጥረታት የፈጠረና(ዮና 1:9, መዝ 33:6-9) ሁሉንም በስልጣኑ ቃል እየደገፈ የሚኖር፥ሰዎች ፊቱን አይተው ሊቆሙ የማይችሉት ታላቅ ግርማ ያለው አምላክ ነው።ታዲያ ይሄ እንዴት አይፈራ!!




እኛ የአዲስ ኪዳን ልጆቹ ደሞ ካጠፋን የሚቀስፈን ወይ ከዛሬ ነገ ያልጠበቅነውን ዱብዳ በላያችን አዘነበው እያልንም አይደለም የምንፈራው።እንዴ መቅሰፍት ምድራዊ፣የታወቀ፣የምንገምተው ግን ያልጠበቅነው ቅጣት እኮ ነው፤ አምላካችን ደሞ ማንነቱን አውቀን የማንጨርሰው ታላቅ ህልውና(BEING) ነው። ይሄ ጌታ ላስተላለፈው ትዕዛዝ ልባችንን ማደንደናችን ነው ሊያስፈራን ሚገባው( ምሳ 28:14)።ወላጆቻችን እንኳን ቤቱን አፅድታቹ ጠብቁን ሲሉን " ቆይ ሲመቸኝ እሰራለሁ አረጋጉት" ያለ ከመሀከላችን ይኖራል ብዬ አላስብም።የቅድስና ጥግ ደርሰናል ባልንበት ቀን እንኳን ፊቱ ስንቀርብ በአክብሮተ ፍርሐት(AWE) መሆን አለበት፤ ምክንያቱም የኛ ተራ ማንነት ዋጋ የኖረው ከራሱ የተነሳ ስለሆነ ልናቀለው አንችልም።

ኢሳ 66:2 ላይ" በቃሌ ወደሚንቀጠቀጠው እመለከታለው.."ያለው ከማንነቱን ማወቅ የመነጨ የቃሉ ፍርሃት ያለበትን አክብሮት ይናገራል።ዕብ 12:21 ላይ "ሙሴ እጅግ እፈራለው እንቀጠቀጥማለው" ያለው ስሜታዊ የሆነ የውስጥ መንቀጥቀጥ ተሰማኝ እያለ አይደለም፥ የምር አካሉ ይንቀጠቀጥ ነበር። ከእግዚአብሔር ጋር እንደ ጓደኛ ሲያወራው የነበረው ሙሴ እንኳን 10ቱ ትዕዛዛት ሲሰጡት እየራደ ነበር፥ እግዚአብሔር ከስትንፋሳችን በላይ ቢቀርበንም አንለምደውም። ዮሐንስም "እንደሞተ ሰው ሆኜ ወደቅሁ"(ራዕ 1፥17) ያለው የኢየሱስን መገለጥ ሊሰጠው የሚችለው የአክብሮት(ፈሪሀ እግዚአብሔር) መገለጫው ነው። ታላላቆቻችን በር ከፍተው ሲገቡ "ኖር" ተብሎ ይቆማል ታዲያ ለዚህ ክቡር አምላክ እንደሞተ ሰው በፊቱ መውደቅ ያንሰዋል።

እውነት እላችኋለው አምላካችን የሚፈራ ነው፤ ለኛ መድሀኒታችን እና አባታችን ከመሆኑ በፊት አምላክ ነበረ፥ አምላክነቱን በአባትነቱ አልተካውም።ቀድሞም አምላክ አሁንም አምላክ ዘላለምም ብቸኛ አምላክ ሆኖ ይኖራል። በልጁ በኢየሱስ ልጅ የሆንበትን ብስራት ሳናገኝና ከኛ ጋር የአባትና ልጅ ትስስር ከማረጉ በፊት፥ ብናምነውም ባናምነውን፣ ላመኑትም ለካዱትም አምላክ ነበር፤በደሙ ሲዋጀን የአባትና ልጅ ጉድኝት ተጨመረልን እንጂ ቀድሞ አምላካችን ነበር። ስለዚህ አምላካችንን የምንፈራውን ያህል ለአባትነቱ በፍቅር እየተገዛን እንኖራለን። ስላዳነን እንወደዋለን አምላክ ስለሆነ እንፈራዋለን፥ ምክንያቱም አህዛብ እንኳን ሊፈሩት የተገባው ስለሆነ።አጋንንትም የፍፁምነቱንና የሀይሉን ታላቅነት ጠንቅቀው ስለተረዱት እየተቃወሙት ይፈሩታል(ያዕ 2:19)።

# ግሣጼ

አሁን አሁን የአዲሱ ኪዳን ልጆች አባትነቱን እና መሀሪነቱን ሞቅ አድርገን ካወራነው ኋላ የመፈራቱን እና አምላክም የመሆን ምስጢሩን እናለባብሰዋለን። የጌታ ማንነት አይጣረስም አይለወጥምም፤መሀሪና አፍቃሪ መሆኑ ቁጡና የሚቀጣ መሆኑን አያስቀርም(ሮሜ 11:19-21)፣ ወዳጅና አባት መሆኑ አምላክ፣ጌታና ገዥ መሆኑን አይለውጥም(ዮሐ 13:13,1ዜና 29:12)፣ ቸርና ሩህሩህ መሆኑ የሚባላ እሳት መሆኑን አይሸፍንም(ዕብ 12:29, ዘዳ 4:24)።
በአዲስ ኪዳን በሰፊው ምህረቱና ፀጋው መገለጡ በቤቱ ሆነን ያለ ጭንቀት(ሥቃይ) ማንነቱን እንድናውቀው እንጂ የአምላክነቱን መፈራት እንድንዘነጋው አይደለም።እስቲ የአስፈሪውን አምላክ የቁጣ ዝናብ በራሱ በአስፈሪው ጌታ ጥላ ዉስጥ ተሸሽገን ማለፋችንን ጠንቅቀን እናስተውል ቀጥሎም በጥላውስር በአጽንኦት የሚወራው ይሄው ዱብዳ ታሪክ ሲሆን አስቡት። ይህን እውነት እንዳንዳፈር እግዚአብሔር ይጠብቀን.

**ስሙን አቀለልነው እኮ**።የአምላካችን ስም፥ አጋንንት የሚርዱለት ስም፣ አህዛብ እንኳ ስሙን የሚፈሩት(መዝ 102:15, ኢሳ 59:19, 24:15)አህዛብ አይደለሁ እንዳትሉኝ ደሞ)፣ከስም ሁሉ በላይ የሆነ ስም ያለው ነው። እስቲ ስንቶቻችን ነን አክብሮታዊ ፍርሀት ባለበት ስሜት ስሙን የምንጠራው (ከዝማሬዎቻችንና ፀሎቶቻችን ዉጪ የሆኑ አላግባብዊ የስሙ ጥሪዎች ይታሰቡ)? የአስተማሪዎቻችንን ስም እንኳን በወሬ መሀል ድምፃችን አሟልጮን ከጮኸ፥ ድምጼ ምነው ከእንጥሌ ተጋጭቶ ሳይሰማ በቀረ እንላለን እኮ። የዝህን ታላቅ አምላክ ስም ግን እንደ ፍራፍሬ ከላይ እየቀነጠስን በየወሬው፣በየቀልዱና በየምሐላው ምናወርደው ሲሆን ያሳዝናል።በአይሁድ ዘንድ ያህዌ(JEHOVAH :-HEB-JHVH ) የሚለው ስሙን አሁንም ድረስ ይህን ስም መጻፍና መጥራት እንደ ድፍረት ይቆጠራል።እናም ቃለ እግዚአብሔርን እያካፈሉ ወይ እየተወያዩ ሳለ ይህ ስሙ ጋር ሲደርሱ "አዶናይ(ADONAI) በሚለው ስሙ ይተኩታል። ለምን ሆነ? ዘሌ 24:16፣ዘፀ 20:7 ያዘዘውን በመፍራት። ፍርሀታቸው ልክ ባይሆንም ለስሙ ያላቸው ክብር ግን የሚያስደንቅ ነው።ተደንቀን ግን አንለፈው፥ አግባብነት ሰጥተነው እንወርሰዋል።

# ግሠፎ

**መድረኮቻችን ሊፈሩና ሊከበሩ ይገባል።**
አገልጋዮች(መሪዎች፣አስተማሪዎች፣ ዘማሪዎች ወዘተ..) መድረኩ ላይ የሀያሉንና ድምፁ ያልተዋጠውን፣ሰው ያላጣውን አምላክ መልዕክት ሊያስተላልፉ እንደሚወጡ፥እንደው የራሳቸውን ሀሳብና ዲስኩር አስደምጠው እንዳይወርዱ(በዛም ጌታን እንዳይዳፈሩ) አግባብነት ያለው አክብሮተ ፍርሀት ለጌታ ሊኖራቸው ይገባል።ጌታ የፈለገው ተትቶ አገልግሎት የለምና ምን ልናገር? ምን ልዘምር? እንዲሉ ያስፈልጋል።ስለገባን ብቻ ኣንሰበክ፥ ስላወቅንም ኣንዘምር።በፀሎት መሰዊያችን ላይም ስንቀርብ አክብሮት ፍርሀት በተሞላበት ስሜት ፊቱ ሆነን እንጠይቀው። ምን ትፈልጋለህ አባት ሆይ?
**በፍቅር እንጂ በሰቆቃ ኣይደለም።**ይሄ ፍርሀታችን ግን በፍቅር የሆነ ፍፁም ደስታና መደነቅ ያለበት ሊሆን ተገቢ ነው።አለዚያማ የመዳናችን ምስጢር ምኑ ጋር ነው። ከሱ መራቃችን የጭንቀትና ህመም ያለበት ፍርሀት ሲያመጣብን ወደርሱ ጉያ መቅረባችን ደሞ ረፍትና ሰላም ያለበት፥ ፍቅርን የተሞላ ፍርሀት በልባችን ያፈሳል( ነህ 1:11, ኢሳ 11:2-3,1ዮሐ 4:18)።
መፅሀፍ ቅዱስ እና ፍጥረት ስለ እግዚአብሔር ማንነት ከሚነግሩን ጋር የእግዚአብሔር ስሙ እኩል ነው።ስሙን እንደማንነቱ ማክበር ይሁንልን. **አሜን!!**
ንጉሴ ቡልቻ በጽሁፎቻቸው መጥለቅያ በፀሎት ሚዘጉባት ልምድ አላቸው እኔም ከነሱ ልኮርጅና በፀሎት ልዝጋው።
አቤቱ ስለመከርከን እናመሰግናለን።
በቤትህ ዉስጥ በአባትነትህ ፍቅር ስንቦርቅ፥
የአምላክነት መፈራትህን እንዳንዘነጋው እርዳን።
ለክቡር ቃልህ በፍቅር እየራድን፥
ሁሉን አጥርተው በሚያዩ አይኖችህ ፊት መታየት ይሁንልን።
ስምህ ማንነትህ ነውና እንፈራው ዘንድ እንውደደው።
ለአምላክነትህ እንደ ህዝብ፣ለጌትነትህ ደሞ እንደባርያ
ለአባትነትህ እንደ ልጆች ሆነን የምንቀርብበት ልቦና ስጠን።
ይህ ላንተ ክብር ፥ ለኛ ለልጆችህ ደሞ ጥቅም ስጥል አድርገው።
**ኣሜን!!**

# THE CHOSEN



## Movie suggestion

The Chosen is a television drama based on the life of Jesus of Nazareth, Created, directed and co-written by American filmmaker Dallas Jenkins. It is the first multi-season series about the life of Jesus, and season one was the highest crowd-funded TV series or film project of all time. The series' creators stated that they had hoped to distinguish the new series from previous portrayals of Jesus by crafting a multi-season, episode-based story. The series portrays Jesus "through the eyes of those who met him". In addition to VidAngel  and its own app, the series airs on several streaming services.

# ራስን መግዛት

ሰላም እንዴት ናችሁ አንባቢዎች፣ በዚህች አጭር ፅሁፍ ስለ አንድ የመንፈስ ፍሬ ላስነብባችሁ ወደድኩ፡ ራስን መግዛት

ራስን መግዛት የሚለውን ቃል በእንግሊዝኛ፣ በአማርኛ፣ በግሪክ፣ በግዕዝ ሁሉ አልቀረኝም ለመተርጎም ስሞክር፤ እንዲህ ነው ብዬ የምገልፅበት አንድም ወጥ አርፍተነገር ላገኝ አልቻልኩም። ሆኖም ግን ሁሉም ነገር መገኛ አለውና ስርወ ቃሉን ለመግለጽ ያክል፡ በእንግሊዘኛው ራስን መግዛት "TEMPERANCE" ወደሚለው የሚተረጎም ሲሆን እንግሊዝኛው ቃል "TEMPERANCE" ደግሞ ከላቲኑ "TEMPERARE/ TEMPERANTIA" ከሚለው የሚመዘዝ ነው። መጽሐፍ ቅዱሳችን አስቀድሞ የተፃፈባቸውን ቋንቋዎች ከግምት ስናስገባ ደግሞ ራስን መግዛት/ TEMPERANCE የሚለው ቃል በግሪኩ በሁለት የተወከለ ነው። የመጀመሪያው "SOPHROSUNE" የሚለው ሲሆን ይህም በሰፊው SELF RESTRAINT/ራስን መቆጠብ ወይም ማገድን የሚያመላክት ነው። በመጽሐፍ ቅዱሳችን ብዙ ግዜ ጥቅም ላይ የዋለው "ENKRATEIA" የሚለው አቻውም በራስ ላይ የሚደረግ ቁጥጥር/ ራስን ያማከለ ስነስርዓትን ማራመድን ያመላክታል።

ወደ እኛው ወደራሳችን ቋንቋ ስንመጣ ደግሞ ራስን መግዛት ከሁለት አማርኛ ቃላቶች የተመሠረተ ጥምር ቃል እንደሆነ ገና ስንሰማው መረዳት እንችላለን። "ራስ" እና "መግዛት" ። "ራስ" በዚህኛው አገባብ ከአንገታቸን በላይ ያለውን የሰውነት ክፍላችንን ማለትም እንዳልሆነ እንረዳለን። "ራስ" በዚህ ጥምር ቃል ውስጥ የሚያገለግለው ማንነትን/ እኔነትን/ የራስ ስሜትን በመግለጽ ሲሆን "መግዛት" የሚለው ቃል ደግሞ ዋጋን ከፍሎ የራስ ማድረግን ሊገልጽ ይችላል። ማንኛውንም ሰው ብንጠይቅ ደግሞ ራስን መግዛት የአካባቢን የባህልና ወግ ስርዓት በተጨማሪም የእግዚአብሔርን ህግ ላለመጣስ የሚሰመር መስመር ሆኖ እናገኘዋለን።

መጽሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን አውድ ስንከተል ራስን መግዛት ልከኝነትን፣ ትህትናን ፣ አስተውሎትንና እነዚህን የመሰሉ ምግባሮችን ገንዘቡ ያደረገ የመንፈስ ፍሬ እንደሆነ እንረዳለን። ታዲያ ይህን ሁሉ መንገድ ተጠቅሜ ራስን መግዛት ይህ ነው ብዬ መተርጎም ከቻልኩ ራስን መግዛት ለእኔስ ምንድነው?

ሰው የትኛውንም አይነት ግዢ የሚፈጽመው/ ዋጋን የሚያወጣው ለሚያስፈልገው መገልገያው ብቻ ነው። እኛ ክርስቲያን የሆንን ደግሞ ራሳችንን የምንገዛው መጀመሪያም የተገዛን ስለሆንን ነው። ስጋችንም ሆነ መንፈሳችን፣ እኛ ብለን የምንጠራው ማንነታችን ሁሉ ከእግዚአብሔር የተቀበልነው፣ ለእግዚአብሔር ክብር የሆነ የእግዚአብሔር የራሱ መገልገያው ነው። በ1ኛ ቆሮንቶስ 6 "በዋጋ ተገዝታችኋልና የራሳችሁ አይደላችሁም" ካለኝ የእግዚአብሔር ቃል ይህ አንድን ጥያቄ እንድጠይቅ ያደረገኛል። የራሴ ያልሆነውን ማንነቴን እንዴት አድርጌ፣ ከማንስ ነው የምገዛው?

እግዚአብሔር ዋጋን ከፍሎ የራሱ ሲያደርገን በራሳችን ላይ ምንም ስልጣን የሌለን ፈቃድ አልባ ባሪያዎች አድርጎ አይደለም። ሽክምና ቶሎ የሚከብ ሀጢአት በሞላበት በዚህ ምድር እስካለን ድረስ ሰውነትችንን መቆጣጠር አስፈላጊ ነው። ለዚህ ነው እግዚአብሔር ዋጋን አውጥቶብኛል ስል እንዲያውም ራሴን ለመግዛት የበለጠ መታመን ያለብኝ። ራሴን የምገዛው ለእግዚአብሔር፣ ራሴን የምገዛው ከአለም።

ራሴን የምገዛው ትግል ስላለብኝ ነው። ራሴን የምገዛው ትግሉን ማሸነፍም ጭምር ስላለብኝ ነው። ትግሉ ደግሞ የራሴው ነው። ይህ ሁሉ ደግሞ ለጦር ያስከተተኝን ደስ አሰኝ ዘነድ። ጳውሎስ ይህንን ትግል በሮሜ 7 ላይ "በውስጡ ሰውነቴ በእግዚአብሔር ሕግ ደስ ይለኛልና፥ ነገር ግን በብልቶቼ ከአእምሮዬ ሕግ ጋር የሚዋጋውንና በብልቶቼ ባለ በኃጢአት ሕግ የሚማርከኝን ሌላ ሕግ አያለሁ" እያለ ይገልጸዋል።

ይህ ራስን ከራስ ጋር የሚያጋጥመው ትግል ነው ራስን መግዛትን መሳሪያው ያደረገው። ወደ እግዚአብሔር ህልውና፣ ወደ ውበቱና ግርማው፣ ወደ ማንነቱ እንድጠጋ፣ እርሱን እንድመስል አልፎም በእኔነቴ ሁሉ እርሱን አክብሬ ደስ እንዳሰኘው ራሴን መግዛቴ ይህን እንዳላደርግ ከሚያግደኝ ሁሉ መዋጊያ መሳሪያዬ ነው። ስጋዬን ጎስሜ ኢሚዛናዊ ሊሆን የሚቃጣውን ፍላጎቴን የምገራበት ማረሚያዬ ነው።

ራስን መግዛት የሚጀምረው ራስን ከማወቅ ነው። ወደ እግዚአብሔር ባልተጠጋን፤ ቃሉ ጓደኞችን፣ ድምፁ ሙዚቃችን እስካልሆነ ድረስ፤ ቅርንጫፎቻችንን ገርዞ እስቅናቆጠቁጥ ካላረመን፤ በምኞትና በሀጢአት የመውደቅ ዝንባሌአችን ትልቅ እንደሆነ እንዲሁም ሀጢአትም ሆነ የምኞት ዘር በውስጣችን ከተዘራ በራሳችን ብቻ እምቢ ብለን እንደማናመልጠው ከመረዳት የሚጀምር ነው። የእግዚአብሔር ቃል ከሀጢአት ሽሹ ብሎ ብቻ የማያበቃውም ለዚሁ ነው። የሚያስመልጠው ሽሽቶ "መስቀሉንም የማይዝ በኋላዬም የማይከተለኝ ለእኔ ሊሆን አይገባውም" ያለውን ለመከተል መሮጥ ነው።

ራስን መግዛት የሚለውን ቃል ስንሰማ ቶሎ ወደ አእምሮአችን የሚመጣው ሀሳብ ራስን መግዛት ከዝሙት፣ ከመዳራት፤ ራስን መግዛት ከሱስ፣ ከምኞት፣ ከጥልና ክርክር እና ከመሳሰሉት በጭንቅላታቸን ከበድ አድርገን ከምንስላቸው ድርጊቶች ነው። ራስን መግዛት ግን ይህ ብቻ አይደለም። ጥቃቅን ብለን ትኩረት ከማንሰጣቸው ነገሮችም ነው። ራስን መግዛት ከግብዝነት፣ ከፈራጅነት፣ ነጭ ከምንለው ውሸት /WHITE LIE/፣ ፍቅር ከሌለው ህይወት፣ ከመሳሰሉት።

በተጨማሪም የምንበላውንና የምንጠጣውን እንደምንጠነቀቅ ሁሉ ወደ ልባችን የሚገባውንም መጠንቀቅ አለብን። ከምንሰማው፣ ከምናየው፣ ከምናስበው፣ ከምናቅደውና ከምናልመው ጅምር። ራስን መግዛት ነፍሳችንን ከምናበላዉ መንፈሳችንን ከምናጠግበው ነገር ተከፍቶ ከዚያው ይቀዳልና።

ደግሞም ራስን መግዛት ከማድረግ ብቻ ሳይሆን ካለማድረግም ነው። ከስንፍናና ስራ ፈትነት፣ ታካች ከመሆንም ራስን መግዛት ያስፈልጋል። ራስን መግዛት ከመልካም ነገርም ሊሆን ይችላል። መብቴ ነው ብዬ ካስቀመጥኩት ነገር፤ ነፃነቴን አሳልፎ መስጠት ነው። ራስን መግዛት ስጋን አለመብላት ነው። የስጋ ጥቅሜን ለመንፈሳዊው ማስገዛት። የአሁን ደስታዬን ለዘለዓለሜ መለወጥ ማለት ነው።

ስለዚህ ራስን መግዛት ከማድረግ መቆጠብ፣ መልካምንም ቢሆን ለበለጠው መልካም አሳልፎ መስጠት እንዲሁም ምንም ካለማድረግ መጠንቀቅ ከሆነ በአጭሩ ለመግለጽ፡ ወደ አንዱ እንዳንጎብጥ ራስን ቶሎ ቶሎ ማረቅ ነው።

ሀሳቤን ለመጠቅለል ራስን መግዛት በዚህ ምድር እስካለን ድረስ እለት እለት በአስተውሎት ልናደርገው የሚገባ ድርጊት ነው። ቃል ለተገባልን ርስት የአኛ ባልሆነ የእንግድነት ቤት ራሳችንን የምንገራበት የሚደርቅ ልምጭ፤ በትግልና በውጊያ የተሞላውን ጊዜያዊ ማንነት ትግል ለሌለው ዘለአለማዊ ፍፅምና ማዘጋጃ መንገድ ነው።

ይህንን ለእኛ ሳይሆን በእኛ ለሚከብረው ለእግዚአብሔር ስንል እናደርገዋለን። በላያችን የተሸከምነውን ቅዱስ ስም ቅዱስ ማህተም እናከብር እናስጠራ ዘንድ ነው። ደግሞ ታግለን መና አንቀርም። የማያረጅ፥ የማይዝግ ሽልማት፤ ብል የማይበላው፥ ዝገት የማያጠፋው መዝገብ፤ በሰማይ ያለ፥ በእጅ ያልተሰራ ሰማያዊ ርስት ተስፋችን ነው።

# የዜማ ቅምሻ



ሙሉ ፡ መስዋዕት ፡ እንከን ፡ የሌለው ፡ ኦሆ
ለአማልክት ፡ አምላክ ፡ ይዣለው ፡ ኢኽው ፡ አሃ
የማያነክስ ፡ ወይ ፡ ያልታወረ ፡ ኦሆ
ለጌቶች ፡ ጌታ ፡ ለተከበረ ፡ አሃ

በፊቱ ፡ የተወደደ ፡ በፊቱ ፡ ከቶ ፡ ያልተናቀ
ሊያሸተው ፡ በአምላኬ ፡ ዘንድ ፡ ዘወትር ፡ የተናፈቀ
ቅዱሱም ፡ ሕያው ፡ መስዋዕት ፡ እራሴ ፡ ነው ፡ ሰውነቴ
ላፍስሰውና ፡ ልሰዋው ፡ ደስ ፡ ይበለው ፡ መድኃኒቴ

አዝ፡- ለአምላኬ ፡ ምሥጋናዬን ፡ እሰዋለሁ
ለንጉሡ ፡ ስዕለቴን ፡ እከፍላለሁ
ይህ ፡ ለእኔ ፡ ሥራዬ ፡ ነው ፡ ልማዴ
በወቅቱ ፡ ክብርን ፡ መስጠት ፡ ለውዴ
ይሄ ፡ ነው ፡ ልማዴ (፫x)

ሙሉ ፡ ለሙም ፡ ጭሶ ፡ የሚቃጠል ፡ ኦሆ
በዙፋኑ ፡ ላይ ፡ እሰይ ፡ የሚያስብል ፡ አሃ
ያለቁጠባ ፡ ያለ ፡ ስስት ፡ ኦሆ
በማደሪያው ፡ ላይ ፡ ይሸተትለት ፡ አሃ

ከነፍሴ ፡ ከፍፁም ፡ ደስታ ፡ የነፍሴ ፡ ነው ፡ ከፍቃዴ
በጠዋትና ፡ በማታ ፡ የምሰዋለት ፡ ለውዴ
የተመረጠውን ፡ መስዋዕት ፡ ከስቡ እና ፡ ከበኩሩ
አምላኬን ፡ ደስ ፡ ካሰኘው ፡ ይኽው ፡ ለዝናው ፡ ለክብሩ

የደመናትን ፡ ድንበር ፡ የሚጥስ ፡ ኦሆ
ወደ ፡ ማደሪያው ፡ የሚገሰግስ ፡ አሃ
የተወደደው ፡ ውድ ፡ ምሥጋና ፡ ኦሆ
የተገባው ፡ አምላክ ፡ ነውና ፡ አሃ

በምድር ፡ እስካለሁባት ፡ እስከ ፡ ኖርኩባት ፡ ዘመኔ
የሚገባውን ፡ በሙሉ ፡ አላጓድልም ፡ ከእኔ
በማንኛውም ፡ ሁኔታ ፡ በማንኛውም ፡ ሰዓት
እርሱ ፡ ይቀበለኝ ፡ እንጂ ፡ አልሰለችም ፡ መሰዋት

# ከተነሀያም ከተነያያም

## ነገረ ታይታኒክ

ከመቶ አመታት በላይ ያስቆጠረ የብዙዎች መነጋገርያ የሆነ ትልቁ አደጋና የሰውእልቂት የታየበት የገናናዋና ስመጥር የሆነች አርኤምኤስ ታይታኒክ(RMS TITANIC) መርከብ ወደ 3ኪሜ በላይየሚሆን ውቅያኖስ ውስጥ ሳታንገራግር ከ1517 በላይ የሚሆን ነፍስ ጋር የምዝቀጧ ነገር አይረሳም።እውነትእንነጋገርና ታይታኒክ የሚለውን ስታነቡ፥በብዙዎቻችን ምናብላይ ቀድሞቂብ የሚለው በጄምስ ካሜሮን(JAMES CAMERON)የተደረሰው እናዝነኛነትን ያተረፈውን እንዲሁም ሊዮናርዶ ዲካፕሪዮ(LEONARDO DICAPRIO)እናኬት ዊንስሌት(KATE WINSLET) በመርከቧ አፍንጫ ላይ እጃቸውን ዝርግተው ፥በወገብ ተቃቅፎሽ ያንን የውቅያኖስ ንፋስ እየቀዘፉት የታዩበት ወሸነኔ(ROMANTIC) ትዕይንት እንደሆነ ጥርጥር የለውም። እኔም ከማሰብ አልፌ ለመጻፍ በቅቻለው። ይህንፅሁፍ ግንእንድጽፍ ያነሳሳኝ ከተሳፋሪዎቹ አንዱ የነበረው የወንጌላዊው ጆንሃርፐር የመርከብ ቆይታ ነው።

ስለሱ ከማንሳቴ በፊት የመርከቢቷን ጉዳይእዚህ ብዬልቋጨው።አርኤምኤስ ታይታኒክ በሚያዝያ 10 ከሳውዝ ሀምፕተን(SOUTHAMPTON)ጉዞዋን ስትጀምር፤ እስከዚያ ዘመንድረስ በሰውእጅ ከተሰሩ ተንቀሳቃሽ ነገሮች ሁሉተወዳዳሪ የሌላት ግዙፍ መርከብ፥በሺዎች አጀብነበር የተቸኘችው። በወቅቱ በታይታኒክ ላይተሳፍሮ መሄድብቻ ሳይሆን ስትጓዝ መሸኘትም አጓጊነበር። ጉዞዋን ስትጀምር ወደ2224 የሚጠጉ ነፍሳት በውስጧ አቅፋ ነበር። ከመነሳቷ በፊት የመርከቧ ባለቤት ጆን ፒርፖንት ሞርጋን(JOHN P. MORGAN)፥በምርቃት ስነስርዓቱ ላይ በንግግሩ ፍፃሜ ፅርፈት(ስድብ) የተሞላ አባባል ሰነቀረ፤ በግዝፈቷ፣ ውበቷ፣ አጠቃላይ አሰራርና ጥንካሬ በፅኑየተደመመው ሞርጋን "ታይታኒክን ራሱ እግዚአብሔር እንኳ ሊያሰምጣት አይችልም" ሲል ተመፃደቀ። የመስመጧ ጉዳይግን የጌታቁጣ ይሁንአይሁን ራሱእግዚአብሔር ብቻነው ሚያቀው። ታዲያ ከተነሳች በ4ኛው ቀን በሚያዝያ 14, 1912 ዓ.እ ታላቋመርከብ ከበረዶ ቋጥኝ ጋር ተላትማ በአትላንቲክ(ATLANTIC) ውቅያኖስ ዉስጥሰጠመች።1517 በላይሚሆኑ ነፍሳት ሲጠፉ ፤ 700 የሚሆኑ ደሞ በህይወት አድን ጀልባዎች(LIFE BOAT) ላይ በመሆን ሲተርፉ፥7 ሰዎችደሞ ከውሀው ውስጥ ከብዙ ቆይታ በኋላ ተመልሰው በመጡ ህይወት አድን ጀልባዎች ተወስደው መትረፍ ችለዋል። ከነዚህ 7ቱሰዎች ስቲቭክሬይን(STEVE CRAIN) የተባለው በምስክርነቱ በተናገረውና በሌሎች ትሩፏን ምስክርነት ላይ የተመሰረተ ታሪክ ነው።

# ክቡኑሀያም ክቡሁያያም

ከተሳፋሪዎቹ አንዱ የ39ዓመቱ ጆንሀርፐር(JOHN HARPER) ከ 6 አመት ልጁ(ናና/NANA የተባለች) ጋር ወደ ሽካጎ(CHICAGO)ለመሄድበመርከቧ ተሳፈረ።በሽካጎ ባለ ትልቅ ቤተክርስቲያን ውስጥ የቤተክርስቲያኗ መጋቢ ሆኖ እንዲያገለግላቸው በቀረበለት ጥሪ ወደዛ አቀና።ጆን በ17 ዓመቱ በመንገድ ዳር ወንጌልን መስበክ የጀመረ ሲሆን ከ5-6 ዓመት በኋላ በመጥምቃውያንፈር ቀዳጅ መልዕክተኛነትማህበር ውስጥ ተቀላቅሎ የሙሉ ግዜአገልጋይና ወንጌላዊ ሆነ። ከጥቂት አመት በኋላ የራሱን ቤተ/ክ 25ሰዎች በሚሆኑ ህብረት ጀምሮ 500 ከደረሱ በኋካ ለሌሎች አገልጋዮች አስረክቦ ሌላ ቤተ/ክ መሰረተ።በዚህ አመታት ዉስጥ ሚስቱ ከአጭር የጋብቻ ዘመናቸው ቆይታ ኋላ ናና ከተባለች ህፃን ልጃቸው ጋር ብቻውን ትታው ህይወቷ ያልፋል። በዚህ ሁሉ ዉስጥ ግንወንጌል መስበኩን አላስቆመውም።በዚህአገልግሎቱም ነበር በተጠራበት ቤተ/ክ እንዲታወቅ ያደረገው።

በሚያዝያ 14, 1912 ዓ.እ ምሽት መርከቧ ከበረዶ ቋጥኝ ስትጋጭ፥ለተሳፋሪዎቹከክፍላቸው እንዲወጡ በተደረገው ጥሪ ጆን ሀርፐር ልጁን ይዞ ከወጣ በኋላ በህይወት አድን ጀልባ ላይያሳፍራትና እሱመርከቧ ላይይቀራል። ለሌሎቹም ተሳፋሪዎች "ሴቶች፣ህፃናትና ዘላለማዊ ድነት ያላገኛቹ ወደ ጀልባዎቹ" እያለ ይጣራ ነበር። የመርከቧም ካፕቴይን(CAPTAIN) ባስተላለፈው ትዕዛዝም ልጆችና ሴቶች ቅድሚያ ሲሰጣቸው ነበር።

መርከቢቷ በመስመጥ ውስጥ ሆና እሱ እየተመላለሰ ለቻለው ሁሉ ወንጌልን ይሰብክ ነበር።በመጨረሻምመርከቧ ሆዷመሀል ላይተቆርጦ በሰጠመችበት ሰዓት ብዙዎች ወደውሀው ዘለው በዛ አጥንት በሚሰብር ብርድ በዋና ራሳቸውን ለማዳን ሞከሩ። ጆንሀርፐርም በነበሩት ጥቂት ደቂቃዎች ህይወታቸውን ለማትረፍ ለሚፍጨረጨሩትና ሊሰሙት ለቻሉት ሁሉ የጌታችንንናየመድሀኒታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ወንጌልና የማዳን ብስራቱን በአጭሩ ይነግራቸው ነበር። ሀርፐር ወዲህ ወድያ እየዋኘ ሲመሰክር በትልቅ የመርከብ ጉማጅ ላይ ወደ ተንጠለጠለ አንድ ወጣት ደርሶ በክርስቶስ እንዲያምን አፅንቶ ነገረው።)፤ወጣቱም ኧረበፍፁም ብሎበመለሰለት መልስ ሀርፐር የወጣቱ መስመጥ መቃረቡን አይቶ የራሱን የውሃ ላይ መንሳፈፍያ ጃኬት በማውለቅ "እንግድያውስከኔ ይልቅ ይህ ላንተ ያስፈልግሀል" ብሎ አቀበለው።

# ከነሀብታም ከነድሃም

ከዝያም ወደሌሎች እየዋኘ ወደ ስቲቭ ክሬይን የተባለው ወጣት አመራ፤ ሲደርስም "አንተ ሰው የነፍስህን ድነት አግኝተሀልን?" አለኝ እኔም እረ በፍፁም ብዬመለስኩለት፥እርሱም "በጌታ በኢየሱስ ከርስቶስ እመን አንተም ትድናለህ"(ሐዋ 16:31) አለኝ።ይህንካለኝ በኋላ ወድያው ማዕበሉ ተሸክሞት ነጎደ፤ነገርግን ከጥቂት ቆይታ በኋላና ለመናገርም እንግዳ በሆነ መንገድ የባህሩ ሞገድ መልሶ ወደ አቅራቢያዬ አመጣው። እናም "አሁን ድነሀልን?" አለኝ፥እኔምበፍፁም! በእውነቱ አዎ ለማለት ይቸግረኛል አልኩት። ሀርፐርም በድጋሜ ሐዋ 16:31 በአንክሮ ከነገረኝ በኋላ ብዙም ሳይቆይ ወደ ውሀው ታችኛ ክፍል ሰረገ፤እኔም በዝያ ብቻዬን ቀርቼ በበታቼ ከ3ኪሜ በላይ ጥልቀት ባለው ውሀ ላይ በጣር እየታገልሁ በነበርኩበት ሰቀቀን ውስጥ እያለሁ አመንሁ። ይህም ሰው በምስክርነቱ መጨረሻ "እንግዲህ እኔ የጆን ሀርፐር የመጨረሻ ፍሬው ነኝ" አለ።

በመርከቢቷ ላይ ከተሳፈሩ ዝነኛ ነጋዴዎች፣ፖለቲከኞች፣ምሁራንና የሀይማኖት ሰዎች ወዘተ... ቢኖሩም ዝናና ስም ባይኖረውም እንኳ በእግዚአብሔር ዘንድ ግን የሚታወቅ፣የከበረ ዋጋ በሰማይ ያለው፣የምድሩን ንቆ የሰማይ ዋጋውን ተምኖ የሮጠ(ዕብ 11:36-38) የእግዚአብሔር ባርያ፤ ታይታኒክ ፊልም ከነ ጃክ(JACK)እና ሮዝ(ROSE) ጋር ባይተርከውም ለወንጌል የከፈለው ዋጋ ግን ለብዙዎች መታነጽ ይሆን ዘንድ በሌሎች ሲመሰከርለት ይቀጥላል።እሁንስ እኛባለንበት ዘመን ለወንጌል ያለን ቅናትና ዋጋ ለመክፈል ያለን ዝግጁነት ምን ያህል ነው? ሌላውንስ ከራሳችን አስቀድመን ለማዳን ያለን ሀሳብ? በመርከቡ ላይክርስቲያኑም ያላመነውም ወንድ፥ ሴቶችንና ልጆችን ሲያስቀድም የራሳቸውን ህይወት እንደሚያጡ እያወቁ ነበር።የራሳቸውን ሚስትና ልጆች ብቻሳይሆን የሌላውን ሚስትና ልጅ፣ እህት፣ራሳቸውን ሊያድኑ የማይችሉ የደከሙትን በነሱ ቦታ እያተረፉ እንደነበር አይተናል። የመርከቧ ካፕቴይንም ከ1500 በላይ ከሚሆኑ(ወንዶች ከሚበዙበት) ሰዎች ጋር ከራስ በላይ በሆነ ፍቅር መስዋዕትነት አብሮ ሞተ። በ1ቆሮ 16:13-14 እንዳለው ስራቸውን በፍቅር አደረጉት።

ማጠቃለያ
በሞት ጥላመካከል በአይበገሬነት የወንጌልን አዋጅ ሲያበስር የነበረው ሀርፐር የህይወትን ጥልቅ ትርጉም ያሳስበናል።ህይወታችን የሚሆን ክርስቶስ ከሞት ወድያ አዲስ ህይወት እንደሚሰጠንበፅኑ ይሞግተናል፤ ስለዛም እንድናስብ ይጎተጉተናል።ዛሬም ይህ ድምፅ በየመርከቦቻችን ሆነን በአለም ባህርላይ ለምንቀዝፈውሁሉ የቀረበ አብይና ክቡር ጥሪነው። ለምን? "ሀጥያተኞችን ሊያድን ክርስቶስ ኢየሱስ ወደ አለም መጣየሚለው ቃልየታመነና ሁሉእንዲቀበሉት የተገባ ነው"(1ጢሞ 1:15)። የሀርፐርም የኛም ዘላቂ ጥሪያችን በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም እመን ትድንማለህ የሚል ነው።

# 2012 Fresh carnival



## The Fullness of Jesus

The nation of Israel had suffered under the tyranny of their oppressors. Babylonians, Medes and Persians, Greeks and the Roman Empire had conquered and ruled the Palestine region for centuries. Following the division of a Hellenistic Empire vastly expanded by Alexander the great, the Seleucid dynasty ruled this region. Antiochus Epiphanes IV was one of the Hellenistic king of the Seleucid dynasty. He was the first Seleucid king to use the divine epithets on coins. He declared himself as a manifestation of God. He outlawed Jewish religion traditions, ordered the worship of Zeus as a supreme god and desecrated the holy temple of Jerusalem by offering pig sacrifice. These things led the Jewish people to revolt. The revolt was successfully led by Judas Maccabean. He took Jerusalem and rededicate the temple on Dec. 25,165 B.C. Jews celebrate this annually for eight days. It is called the Feast of Dedication or Hanukkah.

Almost after two centuries had passed since the Maccabean victory against Antiochus Epiphanes IV, another man came to claim himself as a son of God, Jesus. The season was winter and the time came for the festival of dedication at Jerusalem (John 10:22-33). The Jewish leaders gathered around Jesus and asked him. “How long do you keep us in doubt? If you are the Christ tell us plainly”. Then Jesus rebuked their unbelief. He told them that the many good works he did in the name of his Father bear witness of him. Finally, Jesus said to them “I and the Father are one”. Then the Jews became furious. They picked stones to kill him. Not because of his good works but for blasphemy, for claiming himself as God while he was a mere human being –in their human thinking. The Jews were brave enough to defeat that blasphemous king, Antiochus Epiphanes IV. But they didn’t do well this time since they rejected the Messianic king, the true God and eternal life.

Throughout History many individuals and different religions denied that Jesus was a true God manifested in the flesh. For instance, in fourth century A.D. Arius denied the deity of Jesus. In our days Jehovah’s Witness, Islam deny his deity. But the Apostle John tells us in the very first verse of his Gospel that Jesus was with God and he was God. Later on he clearly states that God became flesh and dwelt among us. Our bible plainly states that Jesus Christ is the son of God. The son created everything, the invisible and the visible. He sustains creation by his powerful command. Through him, we have seen the glory of the one and only son. He has the fullness of all divine perfections and attributes of God. In Christ, we his children, are filled from his fullness. Jesus is our righteousness, holiness, redemption and peace. It really gave God pleasure that all of himself is in Christ. From his fullness, he provided everything we need. We need nothing extra. We have Jesus, the son of God and the son of Man.




**ጠይቅ**

እንዴት ነክ ዘመዴ
የየቅሉ ኑሮ ጓዴ
በቦታ በጊዜ በክልል ወሰንም
ተራርቀን ይሆናል በራሳችን አለም
እኔ መቅደሜ አንተ መከተልክ
የሚያበላልጠን ስሌት እንዳይሆንክ
አሁን ባለህበት ሆነክ ፤ ጆሮህን ሰድረክ
ቅለ ልቦናህን እኔው ዘንድ አኑረክ
ዋጋ ሰተህ ስማኝ ልብህን አርግተክ
የዚህ ግቢ ኑሮ ያልተሰየመ
በክፉም በደጉ እያስደመመ
እድሜ የሚያሳልፍ እየተመመ
ባላውቅህም አቋም የሚኖርህ ይመስለኛል
"ሰው ግቢ መጥቶ እንዴት ጣዕም ያጣል
በቀደመው ጊዜ ስንቱን ታዝበናል
ይኼማ ብቻውን ለምን ይከብደናል"
እያልክ እያሰብክም በግልህ ታመነታ ይሆናል
እውነቱን ስነግርክ እዚህ እስከመጣህ •••
ከቀድሞ ሀሳብክ መሸፈት ይኖራል
የጊዜ ብዛቱ ራሱ ይለውጣል
ከቤተሰብ መራቅ የቀድሞውን ጥጋት መሸሻ ማጣትህ
ሰላም እንደሆንክ ብትልም
አዲሱን ፍለጋ ውስጥህ ራሱ ያስማስንህ
በመውጣት መግባት መከራ
የቀለም ፍልሚያ መራራ
ሆኖ ብታገኘው ወጥረህ ተዋግተህ ራስህን አኩራ
ደጉ ህሊናህም መልካሙን ልማድ ማግዶ
ተስፋ ሊሰጥህ እያስመሰለ በውስጡ ሊያጠፋህ ወዶ
ስቃይ ሊጨምርብህ በባሩድ በእቶን እሳት
ሊገናኝህ ከሚፈልግ ሌሊት መርጦ አውደ አመት
ከክፋ ጓደኛ ሽሽ በእርግጥ እርሱ ሞት አለበት
ታላቄ ነው ብለክ መቅደሙን አስበክ
ሁሉንም አትስማው ሰው መሆኑን ረስተክ
ይልቅ አንተም ቻረው ሀሳብ ምክር ካስፈለገው
የማይሰማ ሆኖ ካገኘኸው
ትንሽ ጠጋ አርገክ አርቀህ አስቀምጠው
የመጨረሻ ማሳረጊያ ዋና ምክሬ
ለአንተ ምናገረው እጅጉኑ አክብሬ
ወዳጄ ...
ከወንድሞች ህብረት እንዳትጎድል
አስቸገረኝ ብለህ ጠልተኸው ብትገፋው
በከፋው አለም ውስጥ አንተ ነህ ተጎጂው
ነገሩ የቀይ ዕንቁ ያህል ተመን ነው የተሰጠው
ድካምም ቢበዛ ነፍስህን በውስጡ አኑረው
እዛ ውስጥ ብታገኝ ፍቅር የጎደለው
'ሚያወራውን የማያውቅ ለአፉ ለከት እንኳ የሌለው
የራስህን ቆንጥረህ ህይወትን አስተምረው
ጥሎ መሄድ ከቶ ባህልህ አታርገው
ታዲያ በጉዞ ላይ ሳለህ ...
ውስጥህን መርምር ፈትሽ አመልህን
የማይገጥም ካለ ተማር ነቅለህ መጣሉን
ያን ማድረግ ካቃተህ ጠይቅ ራስህን
ለጌታ የሚገባው ሀቁ ይህ ነውን?
ደጋግመክ ደጋግመክ ደጋግመክ ጠይቅ
በኪሳራ መንገድ ቁልቁል እንዳትማቅቅ
መፍትሔ ፍለጋ አንዴ ቆም ብለህ ማንነትህን ጠይቅ



What has become of whom you made?
Only you can save us;only you can purge.
The evil inside us blooms,
Swelling to swallow Us.
We agonize by the affliction of our nature;
Tormented by what we cannot alter.
We can't shade the dead skin;
walking corpses,to death we are akin.
could not shake off the infestation ;
Of shame,of guilt,of devastation.
Split betwixt good and evil,
Though e'er chose malevolence and vile.
Our chambers are dark,
The stains are black.
It's you who can rid the pest,
Lodged In barracks of our heart,
Dispel forever the evil beast.
Only you can purchase ,
The bond slave driven to death.
By your own blood,sweat and tears;
You have taken our wearies.

The toil,to be enough in God's eyes,
You have replaced it with grace.
O,how great is your benevolence!
That made you choose nails,thorns and the cross.
The void is replaced with bounty,
The despicable is now worthy.
You have become us,
And we have been given yours.

ለፍሬሽ ተማሪዎች ብቻ
ቀድሞ ለመለሰ 3 ተማሪ የካርድ ሽልማት

## Service Teams of Our Fellowship




**Down**

1 “Pure religion and undefiled before God and the Father is this, To visit the fatherless and widows in their affliction...” ( James 1:27)

3 “O come, let us worship and bow down: let us kneel before the LORD our maker.” ( Ps 95:6)

5 “And he said unto them, Go ye into all the world, and preach the gospel to every creature. ( Mark 16:15)

6 “Where no counsel is, the people fall: but in the multitude of counsellors there is safety.” ( Proverbs 11:14)

**Across**

1 “... but in everything by prayer and supplication with thanksgiving let your requests be made known unto God. ( Phil 4:6)

2 “And he hath put a new song in my mouth, even praise unto our God: many shall see it, and fear, and shall trust in the LORD.” ( Psalm 40:3)

4 “Likewise must the deacons be grave, not double tongued...” ( 1Tim 3:8)

Dombo
laza
loly
Abeni
Wonde
Mercy
Dave

## አምደኞች

## Drawing

Robina

## Graphics &Editing

Josh

## Join us

Telegram... t.me/juecsfcounseling
Facebook... juecsfcounselling official
phone number.. 0921118495Or0919320277